ነሀሴ 1998 ዓም

ግልፅ ደብዳቤ

ከኮ/ አስናቀ እንግዳ ( የድሮ ጦር ሠራዊት ባልደረባ፥ ኢትዮጵያዊ)

ለአቶ ለገሠ ዜናዊ የወያኔ ጠቅላ/ይ ሚኒስትር

ካሉበት

ኢትዮጵያን በመቆራረስና በመገነጣጠል፥ ጎዝቧንም በመለያየትና በማጣላት፥ዴሞክራሲን በማፈን ጎሊናዊ ነጻነትን በመግሠሥ፥ የሀገርን ጎልውናና የረጅም ዘመናት ታሪክ በመካድ፥ ሃይማኖታዊ ሥርዓትን ( ቀኖናን) በማፋለስ፥ ባጎልን በመርገጥ፥ የትግራይን ወጣት በራሱ ጥቅም ላይ በማዝመትና በየጦር ምሽጎች እያጋፈጡ የጥይት ቆሎ በማስቃም፥ የሕዝቡን የከተማ ቦታና ቤት እየነጠቁ በመሸጥ የገበሬን ርስት በመውረስ ጤሰኛ በማድረግ ሀገር ወዳድነትን በማጥፋት ምሁራንን ከሥራ እያባረሩ በመግደል ድንቁርናን በማስፋፋት ያረቡን ነጋዴ እያሽሞነሞኑ የሀገሪቱን ሀብት እንዲመዘብር በማድረግ እነዚህንና የመሳሰሉትን ግራና ቀኝ ሳይሉ ጠንክሮ በመታገልና ዘር በማጥፋት የተካኑ ከኢትዮጵያ ጠላቶች የተሰጠዎትን ትዕዛዝ በመፈፀም ታሪክ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ አድርጎ መዝግቦዎታል:: እንደርሶዎ ያለ ይሁዳ ከዚህ በፊት በኢትዮጵያችን አልተፈጠረም ወደፊትም አይፈጠርም::

የወያኔ ጠ/ ም መለስ ዜናዊ!
ከዚህ ቀጥየ የማሳስበዎትን ልብ ብለው እንዲገነዘቡት እጠይቃለሁ::

1ኛ. ወላጆቸዎ ያወጡለዎትን " ለገሠ" የሚለውን ለባህርይዎ የሚስማማውን ስም ትተው፥ በሰፊው አመለካከቱ ለሰው ልጅ መብት ተከራካሪ የነበረውን የ መለስ ተክሌን ስም በመውረስዎ ጠባብ አመለካከተዎ ሊሸከመው የማይችል ሰፊና ጥለቅ በመሆኑ ከአቅመዎ በላይ ነውና እንዳይጨፈልቀዎት ለባኅርይዎ በሚስማማ በለገሠ ይጠሩ:: ምክንያቱም፥ እርሰዎ ሲበዛ ቸር ስለሆኑ ሀገር ቆርሰው የሚለግሱና የሚከፋፍሉ ስለሆኑ፥ "መለስ" የሚለው ስም ፈጽሞ አይስማማዎትም:: ሲለግሱ እንጅ ሲመልሱ አልታዩምና! ምግባር ስምን ይከተላል ነውና፥ ለገሠ የሚለው ስመዎ ይረዳወታልና ይጠቀሙበት::

2ኛ. ታላቂቱን ሀገር ኢትዮጵያን እያስገነጠሉና እየሸነሸኑ በማዳከም ታላቅ ጀብድ የሠሩበትን የድርጅተዎን ስም " ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ" ( ሕወኃት) ብለው የሰየሙት ለታላቁ ለሠፊው ለትግራይ ሕዝብ ባኅርያት ፈጽሞ የሚስማማው ግዙፍ ስህተት ስህተት ስለሆነ በዚህ ስም ባይጠቀሙ መልካም ነው:: ምክንያቱም ሕዝብ ንፉግ ነው:: እንደርሰዎ ለጋስ ሁኖ ሀገሩን ገንጥሉልኝ ብሎ የሚጽፍ አይደለም:: እንዲያውም የትግራይ ሠፊ ሕዝብ ሀገሩን ገንጥሎ ሊሰጥ ቀርቶ፥ ኢትዮጵያን ከፈጠረ በኋላ፥ አልበቃው ብሎ ማዳጋስካርን፥ ደቡብ ዓረቢያን ኑባንና ምሥራቅ አፍሪካን አጠቃልሎ ይዞ ነበረ ነው:: ይህን እርሰዎ ቢክዱት ታሪክ አይክደውም::

3ኛ. የትግራይ ሠፊ ሕዝብ እጅግ ሲበዛ ሃይማኖተኛ በመሆኑ፥ አራት ሺ ቤተክርስቲያኖች ያሉት ለሃይማኖቱ ቀናተኛ ሕዝብ ነው:: ለሃይማኖቱ ብዙ መሷይት ሲከፍል የኖረ በመሆኑ የሰው ደም ለጣዖት አያፈስም:: " ወያኔ" የሚለው ቃል በትክክል የሚስማማው ለእርሰዎ ለገሠ ዜናዊ እና ለማሌሊት የግብር ጓዶቸዎ ብቻ ነው:: ለመሆኑ " ወያኔ" የሚለውን

የመረጡት ትርጉሙን አውቅውት ነው? ከባንርይዎ ጋር የሚስማማ ለድርጅተዎ ወያኔ ብለው ስም ያወጡለት?

ምንም እንኳ “ ወየነ ” ( ዓመፀ) የሚል ከግዕዝ የተወሰደ ቃል ቢሆንም በልማድ ሲሠራበት የኖረው ግን ዝርዝር ማብራሪያ አያስፈልገው። በየጁ አካባቢ ዝናብ እንዲዘንብ፥ በሽታ እንዲጠፋ፥ ቆሌው የሰው ደም መቋደስ አለበት ተብሎ የሁለት መንደር ሰዎች ወደ ወንዝ ወርደው፥ ማዶና ማዶ በመሰላለፍ ሲቆም ወኔ ቀስቃሽ አርሆ ( ወንድም ሴትም ሊሆን ይችላል) ከመካከል ሁኖ እያቅራራ ሲፎክረ ተሰላልፈው የቆሙት ጎረምሶች ወኔ እየገፋቸው ተሶርፈው በጎራዴ እየተጨፋጨፉ እንደ ሁለቱ ተምትቶ ሲወድቅና ደሙ ሲፈስ፥ ቆሌዋ ተቋድሳለች በቃ ብለው ሽማግሌዎች ያቆሙት ነበር። ይህ ዓይነቱ ልማድ በየዓመቱ ይደረግ ነበር።

እናንተ ማሌሊቶች በፈለጋችሁት መንገድ ካልሰየማችሁት በቀር፥ “ ወያኔ” ማለት ለአምልኮ ጣዖት የሰው ደም በማፍሰስ በሃይማኖት( በክርስቶስ ላይ) ማመፅ ወየነ (ዓመፀ) ብለው ሰይመውታል። እናንተም በኢትዮጵያ ላይ ወይናችሁ ድም አፍስሳችኋል። ታዲያ ለሃይማኖተኛው ለትግራይ ሕዝብ “ወያኔ” የሚለው ቃል እንዴት መጠሪያው ሊሆን ይችላል? እናንተ እን ለገሰ ዜናዊ ግን ወያኔ የሚለውን አምልኮ ባዕድ ስም የመረጣችሁት ከባንርያችሁ ጋር ሰምና ወርቅ ስለሆነ ወያኔ ተባላችሁ ልትጠሩበት የተገባ ትክክለኛ ምርጫ በመሆኑ፥ ይባል ይሁን የሚባል ነው። ደም አፍሳሽነታችሁና የእነ ለገሠ ዜናዊ ቆሌዎቻቀችሁ የኢትዮጵያን አንድነትና ብልፅግና የማይወዱ ጠላቶች ስለሆኑ፥ ኢትዮጵያውያን እርስ በርሳቻው ተጋድለው በሚፈሰው ደም መንፈሳቸው ይረካል። የሚፈስሰውንም ደም ጎርፍ ጠራርጎ እየወደሰ ያዳርስላቸዋል።

4ኛ. እርሰዎ ለገሠ ዜናዊ የኢትዮጵያ ጠ /ም ተብለው ሊጠሩ አይገባዎትም። ምክንያቱም፥ “ ኢትዮጵያ የሦስት ሺ ዓመታት ዕድሜ ያለው ታሪክ የነበራትና ያላት ሀገር አይደለችም” ብለው “የኤርትራ ሕዝብ ትግል ከየት ወደየት“ በሚለው መጽሐፊዎ በ1979 ዓም ሕወሓት የሚል የድርጅተዎን ማኅተም አትመው ባሰራጩት መጽሐፊዎም አረጋግጠው በከዷት ኢትዮጵያ እንዴት ተብሎ ነው ጠቅላይ ሚንስትር ሊሆኑ የሚችሉት? የለችም ብል በከዷት ሀገር ላይ ጠቅላይ ምኒስትር መሆን ይገባዎታልን? ወይስ እርሰዎ የፈጠሯት አዲስ ኢትዮጵያ ናት? ለጥያቄው በፍጥነት መልስ እንዲሰጡኝ እፈልጋለሁ። መልስ ባይሰጠኝ ግን ተቀብለዎታል ማለት ነው። መልሰዎ የድሮ ኢትዮጵያ ናት የሚሉ ከሆነ በሠሩት ከባድ ክኅደት ይቅርታ አልጠየቁም። “እንጭት ሆኖ የማይጤስ፥ ሰው ሆኖ የማይበድል” የለምና አጥፍቻለሁና ይቅርታ ይደረግልኝ ብለው አለመጠየቀዎ የሕዝብ ንቀት ስለአለበዎት ነውን? ወይም አሁንም ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር የለችም ብለው እንደገሏት ነዎት? መቼነው ኢትዮጵያዊ የሚሆኑት? አዲስ ኢትዮጵያ ፈጥሬአለሁ የሚሉ ከሆነም እንዴት እንደፈጠሯት አብራርተው ይመልሱልኝ።መቸም በኅዋው( ስፔስ) ውስጥ ካሉት ፕላኔቶች አንዱን አመጣለሁ ብለው ራስዎን የሚያቀል ውሸት አያሳፍረኝም ካላሉ በስተቀር፥ ያጠፏት እንጅ የፈጠሯት ኢትትዮጵያ የለችም።
የከዷት ኢትዮጵያም ሳታውቀዎ፥ እርሰዎም ሳያውቋት 15 ዓመታት ሳትተዋወቁ በሥልጣን ላይ መቆየተዎ ተዓምር ነው። የካሃዲዎችን ሁሉ ክብረወሰን ሰብረዋል። የድሮዋን ኢትዮጵያ ለስትራተጂ ጠላቶቿ ቸርችረው ለግሰውላቸዋል። እንዲህ ነው አንጅ ዕውነተኛ ለገሠ።
አቶ ለገሠ ዜናዊ “ ከትግሬ በመወለዴ እኮራለሁ” ብለዋል። ከትግራይ ቢወለዱም ምግባረዎ የተግራይ ሰው አያደርገዎትም። ከትግራይ መወለደዎ የሚያኮራዎ ቢሆንማ፥ የትግራይ ወኔ፥ ጀግንነት፥ አትንኩይ ባይነት፥ ታላቅነት፥ ዕውነተኛነትና ሠፊ አመለካከት ይኖረዎት ነበር። እርሰዎ ግን ትግሬዎች የገነቡትን ሀገር የሚቆራረጡና የሚከፋፍሉ፥ ሠፊ አመለካከት የሌለዎት ጠባይ ጎሰኛ ስለሆኑ፥ ዓላማዎና ተግባረዎ የትግራይ ሕዝብ አያደርጉዎትምና እራሰዎን የለኩበት አዕምሮ ትክክል አይደለም። አቶ ለገሠ፥ ለመሆኑ የፃፉትን ያስታውሱታልን?

“ የአክሱም መንግሥትም ቢሆን በማንኛውም ወቅት መላውን የዛሬይቱን ኤርትራ ይቆጣጠር የነበረበት ወቅት አልነበረም” ብለው ዓለም ያወቀውን፥ ታሪክ የመዘገበውን የካዱ ያዕምሮ ድሃ ሲሆኑ፥ የትግራይን ታሪክ እያጠፉ፥ እንዴት ብለው ነው በትግራይነተዎ ሊኩሩ የሚችሉት? ወይስ አክሱም የትግራይ አይደለችም ማለተዎ ይሆን? የእርስዎ ኅሌና አይሰማው እንደሆን እንጅ፥ እኮራባታለሁየ ሚሏትን ትግራይን እኮ ታሪኳን፥ባሕሏን፥ መንግሥቷንና ሕዝቧን በማጥፋት ላይ ነው ያሉት። ለመሆኑ፥ ትግራይ ማለት አክሱም መሆኑን ኢትዮጵያ ማለትም አክሱም መሆኗን ማስታዎስ አይችሉምን? እርስዎ የገነጠሏት ኤርትራ እኮ የአክሶም ማድቤትና ዕልፍኝ የነበረች ናት!

5. አቶ ለገሥ ዜናዊ የኢትዮጵያ ሕዝብ በዴሞክራሲያዊ መብቱ ተጠቅሞ በግንቦት ወር 1997 ዓም በነበረው ምርጫ ይመሩኛል ያላቸውን ሰዎች ቢመርጥ ሁሉንም ጠቅልለው ወኅኒ ቤት በማጎሮዎ እርስዎና ጓደኞቸዎ፥ ምን ግዜም ልታገኙት የማትችሉትን ታሪካዊ ዕድላችሁን ገድላችሁታል።

ሕዝብ በዴሞክራሲያዊ መብቶቹ ተጠቅሞ ይመሩኛል ብሎ ለመረጣቸው ሥልጣኑን ብታስረክቡ ኖሮ፥ለፈፀማችሁት ታላቅ በደል ሁሉ ሕዝብ እንደ ይቅርታ ቆጥሮ በሕግ ወጥ መንገድ ዘርፋችሁ ያቋቋመማችሁትን ንብረት እንደያዛችሁ ተዝናንታችሁ በሰላም መኖር ትችሉ ነበር። ጻሩ ግን እንደ ፍርዖን ልባችሁን አደንድናችሁ ወደ አዘቅት የሚወስዳችሁን መንገድ መረጣችሁ። መልካሙን ዕድል አሰናክላችኋል። አሁንም ቢሆን ከተጠቀማችሁበት መልካም ዕድሎች አሏችሁ።

1ኛ. ወህኒ ቤት ያጎራቸችኋቸውን የፖሊቲካ መሪዎችን መፍታት፥

2ኛ. በውጭ ሀገር የተሰደዱትን የፖሊቲካ ድርጅቶች ሀገር ውሰጥ ገብተው አቋማቀቸውን ለሕዝብ እንዲያስረዱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፥

3ኛ. በሀገር ውሰጥ ያሉም ድርጅቶች ያለምንም ተጽዕኖ እንዲንቀሳቀሱ፥

4ኛ. ገለልተኛ የምርጫ ቦርድ ተቋቁሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ የተነጠቀውን ምርጫ እንደገና እንዲያካሂድ ማድረግ የሰላም ዋስትና መሆኑን መረዳት፥

5ኛ. በኢትዮጵያና በኤርትራ ሕዝብ መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት አልነበረም አሁንም የለም። በታሪክ ሰሪነትም፥ በነፃነትም፥ በዘርም፥ በሃይማኖትም/ በዕምነትም፥ በባህልም፥ በቋንቋም፥ በፊደልም፥ በሥነ- ጽሁፍም በምግምባርም፥ በሥነ ልቦናም አንድ ናቸው። ምንም እንኳን ሁኔታውን በሚገባ ያልተረዳችሁት ጥቂት ቡድኖች ኤርትራን ገንጥላችሁ/ አስገንጥላችሁ የራሳችሁን ጊዚያዊ አስተዳደር ብታቋቁሙም፥ ጊዜና ሁኔታ የማይሽረው ጠንካራ ሥነ- ልቦናዊ አንድነት ስለአለ ኤርትራውያን እንደ ባዕድ የሚታዩ አይደሉም። አካላችን ደማችን አጥንታችን ናቸው። በታሪካቸው በጋራ መከራውንና ደስታውን እየተካፈሉ ኖረዋል። እናንተና ሻቢያዎቹ ታልፋላችሁ። የኤትራና የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ቋሚና ዘለዓለማዊ ናቸው።ፖሊቲካና መንግሥታት ሊለዩዋቸው አይችልም ። ነገ እናንተ ስትወገዱላቸው፥ እራሳቸው ተፈቃቅደው፣ ተፈላልገው፥ ተከባብረው ተስማምተው አብረው በሰላም ለዘለዓለም ይኖራሉ። ይህንን ፀጋ እንዲያሳየኝ ቸርና ኃያል የሆነውን አምላኬን እለምነዋለሁ አፀልያለሁ። ይህንንም አይቸ ባለፍ ዘለዓለማዊ ደስታና ዕረፍት አገኛለሁ።

ያ እናንት የቀሰቀሳችሁት የድንበር ግጭትም ይህን ያህል ደም የሚያፋስስ አልነበረም። በከንቱ የፈሰሰው የንፁኃን ዜጎች ደም እጅግ የሚያሳዝንና የሚሰቀጥጥ ነው። መላው ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል አልነበረችምን? ገንጥሉልኝ ብሎ በፊርማ አቤቱታ አቅርቦ ካ/ሰገነጠሉ በኋላ በቆራጭ መሬት ጦር ከፍቶ ወንድማማቾቹን ማፋጀት ምን ይሉታል? አሁንም በአካባቢዎቹ ነዋሪ ሽማግሌዎች ውይይት ሊፈታ ሲችል፥ በልህና በትዕቢት ምንም

መፍተሄ አይገኝም። የእኔ አቅም ሁለት ወንድማማቾች ኤርትራን ኢትዮጵያ ሰላም ወርዶላቸው
አብረው እንዲኖሩ ሁሉን ማድርግ ለማይሳነው ልዑል እግዚአብሔር መፀለይ ብቻ ነው።

እግዚአብሔር ፍጡሮቹን የኢትዮጵያንና የኤርተራን ሕዝብ ይበረክ፥ ይጠብቅ!